# ድሃ በህልሙ ቅቤ ይጠጣል እና ሶስተኛ ደረጃ ተላላኪዎች

By Solomon Tekalign(Tsenat Radio)

የዘወትር ህልማቸው ህዝብና ሃገርን የሚጠቅም ለውጥ ሳይሆን ስልጣን እና ነዋይ የሆኑ ግለሰቦች የቅዥታቸው ማስታመሚያ ምኞታቸው ብቻ ነው፡፡

ድሃ በህልሙ ቅቤ ይጠጣል በሚል ለዚህ ሃሳብ ማጠናከሪያ የአበውን አባባል የተዋስኩትም ለዚሁ ነው፡፡

የኢሳት የሰሞኑ የምኞት ቅቤ ደግሞ የአረቡን አለም አይነት አቢዮት ኢህአዴግ ላይ እናቀጣጥል ሆኗል፡፡

የሰሞኑ የቡርኪናፋሶው ጉዳይ ደግሞ የህልማቸው መነሻ ነው፡፡

እናም ሰዎቹ ከአረቡ አቢዮት ቱኒዚያ፣ ሊቢያ፣ ግብጽ፣ ሶሪያ ተነስተው በቡርኪናፋሶ አድርገው አዲስ አበባ ላይ ስልጣን ላይ ሲቀመጡ እያለሙ የስቱዲዮ ፉከራውን ከፉገራ ጋር በሙዚቃ እያቀለጡ ማስደመጥ ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡

ለመሆኑ ከ3 ዓመት በፊት የጀመረው የአረቡ አለም አቢዮት ከኛ ጋር ምን አገናኘው?

የአቢዮቱ ዋነኛ መነሻ ምክንያት ምን ነበር?

የአመጹ ተሳታፊ ህዝብስ በእርግጥ የፈለገውን አግኝቷል?

እነዚያን የተቀጣጠሉ አመጾች ያነሳሱትስ እነማን ናቸው?

በእርግጥስ ጥያቄው የነሱ ጭምር ነበር ወይስ ደርግ እንደደረገው የህዝቡን ጥያቄ ቀምተው ባቋራጭ ወደ ስልጣን መጡ?

ስልጣኑስ በእርግጥ ከአምባገነን ንጉሳዊያን አሊያም ሌሎች ወጥቶ በእርግጥ የህዝብ ሆኗልን?

ካልሆነስ ለምን?

ምንም ይሁን ምን ደግሞ እኛና እነሱን ምን ያመሳስለናል?

የሚሉና ሌሎች ጥያቄዎችን የምኞት ቅቤያቸውን ከመጠጣታቸው በፊት ቢያስቡት እንዲህ ያለውን የወረደና የተዋረደ እሳቤ ለማራገብ ድፍረቱን ባላገኙት ነበር፡፡

ለማንኛውም ግን በኢሳት የማይነገሩ ጥቂት አስቂኝ እውነታዎችን ላነሳላችሁ ወደድሁ፡፡

እንዴው ነገሩን እንደኛው መንግስቱ ሃይለማርያም በመፈንቅለ መንግስት ወደ ስልጣን መጠው ከ27 ዓመት በፊት ስልጣን የያዙት እና ሰሞኑን በህዝብ አመጽ ስልጣናቸውን የለቀቁት የፕሬዘዳንት ብሌሴ ኮምፓሬ ጉዳይ ቀሰቀሰው እንጅ እንዲህ አይነት አጀንዳ ከ2 ዓመት በፊትም ተነስቶ ነበር፡፡

ያኔ ምርጫ የሚባለውን ነገር ከስም በዘለለ ብዙም የማያውቁት የቱኒዚያው፣ የሊቢያው እና የግብጽ መሪዎች ከስልጣናቸው ሲወርዱና ሃገሩ ሲበጠበጥ ይኸ ነገር ምነው እኛም ጋር በሆነ እና ሃገር በተበጠበጠ ብለው የተመኙ ብዙ ማውራታቸው አይዘነጋም፡፡

ግን ደግሞ የአረቡ አለም ሲበጠበጥ እነዚህ ጽንፈኛ አክራሪዎች የተመኙት ሳይሳካ እነ ግብጽም እየወደቁ እና እየተነሱ አንዴ እየደፈረሱ አንዴ እየጠሩ እንዲሁ በጉራማይሌኛ ብዙ ለውጥ አካሂደዋል፡፡

እኛ ጋር ግን ምንም የተፈጠረም ሊፈጠር የሚችልም ነገር የለም፡፡

ይህም ባለመሆኑ ብዙ የሚገርምም አልነበረም፡፡ ራሳቸው የህልም ጠንሳሾቹ አፍረው ባያውቁም አንድ አጀንዳ አንስተው ሲከሽፍባቸው እንደሚያደርጉት ወደሌላኛው አጀንዳ ምንም እንዳልጠፈጠረ አድርገው ተሸጋገሩ ማለት ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ከሆነ አመታት ተቆጥረዋል፡፡

አሁን ቡርኪናፋሶ ላይ አመጽ እና ብጥብጥ ሲናፈስ ደግሞ ታሪኩን ወደኋላ በመነተት ጉዳዩን አሳማኝ ለማስመሰል ጥረት ሲያደርጉ እየሰማናቸው ነው፡፡

እዚህ ላይ ያኔ እነግብጽ በሆኑት ማግስት እኛም ጋር ሊሆን ነው ሲሉን ቆይተዋል፡፡ አቅም አጠውም ቢሆን ሲሞካከሩት የቆዩት አመጽ ሳይሳካ ቆይቶ ዛሬ ላይ ከአመታት በኋላ ብድግ ብሎ ከማውራት በፊት አስካሁን ያሰቡት ለምን እንዳልሆነ ጭምር ማብራራት ነበረባቸው፡፡

ህዝቡም ሊጠይቃቸው ከተገባ እና መመለስ ካለባቸውም መመለስ ያለበት ካሁን አሁን ተከሰተ ሲሉን የነበረው ነውጥ ለምን አስካሁን ቆየ?

አሁንስ ለምን ታነሱታላችሁ? ይህ ጉዳይዝም ብሎ ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ይከሳል አይነት ወሬ አይሆንባችሁም ወይ?! ተብለው መጠየቅ አለባቸው፡፡

ሌላኛው ነጥብ እነዚህ ህልመኞች የሚያነሱት ወይም ይህንን የብጥብጥ ታሪክ የሚመኙት በምን ምክንያት ነው ብሎ መጠየቅም ተገቢ ይመስለኛል፡፡

እንግዲህ በጽንፈኛው ወገን ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ የህዝብ ነጻነት ......ምናምን ምናምን የመሳሰሉ ጉዳዮች የሉም በሚል ይመስለኛል ከአረቡ አለምም ሆነ ከቡርኪናፋሶ ጋር ሊያመሳስሉን የሚፈልጉት፡፡

እንግዲህ እንደዚህ ከሆነ የነዚህ ነጥቦች ማለትም ቀደም ሲል ያነሳናቸው ጥቅል የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች ትግበራ በተጨባጭ በሃገራችን እንዴት ነው? የሚለው ጉዳይ ሳይታይ መታለፍ የለበትም፡፡

አንደኛውና ትልቁ ቁልፍ የዴሞክራሲ ስርዓት መገለጫ በየትኛውም ዓለም፣ በሰለጠነም ባልሰለጠነም ፣ ባደገም ባላደገም ሃገር ውስጥ ምርጫ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር እኛ ምን እንመስላለን? ህዝቡስ ምን ይላል? ተሳትፎውስ ምን ይመስላል? ብለን ካየን እኛን ከነሊቢያ ጋር ማመሳሰል ምን ያህል የቀቀለለ እና ተራ ሃሳብ ማራመድ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል ባይ ነኝ፡፡

ባለፉት 24 ዓመታት ውስጥ ማለትም አንድም ጊዜ ምርጫ አካሂዶ ሊያውቅ አይደለም ስልጣኑንም ለሲቪል ሳያስረክብ የወረደው ደርግ ከወደቀ በኋላ በሃገራችን 4 ሃገር አቀፍ ዴሚክራሲያዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል፡፡

በአራቱም ምርጫ የመራጩ ቁጥር እያደገ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ ጥሩ ተቃዋሚ አገኘሁ ብሎ ባሰበ ቁጥር ሁሉ ሙሉ በሙሉም ባይሆን ተቃዋሚዎች እየተመረጡ ፓርላማ ገብተዋል፡፡

እዚህ ላይ ያለው ችግሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ምርጫ ፍትሃዊ አይደለም የሚል ሃሳብ የሚያራምዱት ግለሰቦችና ቡድኖች በምርጫ ከተወዳደርሁ የግድ ስልጣን መያዝ አለብኝ፣ ያ ካልሆነ ከኔ በላይ ላሳር አይነት ምርጫው ፍትሃዊ አይደለም የሚሉት ጽንፈኞች ናቸው፡፡

ይኸ ደግሞ ለራስ ከሚሰጥ የበዛ ግምት የሚመጣ ብቻ እንዳይመስላችሁ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ለራሳቸው የላቀ ግምት ለሌላው ያነሰ ግምት ስላላቸው ተብሎ የሚታለፍ የስነ ልቦና ችግር ብቻ ተደርጎም የሚወሰድ አይደለም፡፡

ምክንያም ይኸ ፖለቲካ ነው፡፡ በየትኛውም አለም ውስጥ ያለ የፖለቲካ ጨዋታ፡፡

ይህንን ጨዋታ የሚጫዎቱት ደግሞ ስለማያውቁ ወይም አሁን የምንለውን በኢትዮጵያ ውስጥ እና በአረቡ አለም መካከል ያለውን የዴሞክራሲ ልዩነት እና የመንግስታቱንም ባህሪ አጥተውትም አይደለም፡፡

ይልቁንም ተልእኮ ስለሆነና አውቀው የሚፈጽሙት ተግባራቸው ነው፡፡ በቀለም አቢዮት መንግስትን ከስልጣን ማውረድ፣ ህዝብን እርስ በእርስ ጦር ማማዘዝ፣ ሁሉም ሊፈጽሙት የተዘጋጁት እና ቢችሉ ስልጣን ካልሆነም ደሞዝ የሚያገኙበት የጥፋት ሩጫ ነው፡፡

ለማንኛውም ወደጀመርሁት ማነጻጸር ልሂድና ልዩነቱን ላሳያችሁ፡፡

በሊቢያ፣ በቱኒዚያና፣ በግብጽ እንዲሁም በሶሪያ የተከሰተውን የህዝብ መዓበል ስንመለከት ብዙዎች እንደሚስማሙበት ዋነኛው መነሻ መከንያቱ የመሪዎቹ መረን የለቀቀ አምባገነንነት ቢሆንም ቅሉ በውስጡ ደግሞ ስራ አጥነት፣ የህዝቡ የልማት ፍላጎት፣ የኑሮ ውድነት እና የመሳሰሉ ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችም ነበሩበት፡፡

እናም የህዝቡን ሰፊ የዴሞክራሲ እና የልማት ጥያቄ ይዘው ጥቂቶች ህዝቡን ለንቅናቄ አነሳስተውታል፡፡

በሊቢያ ጋዳፊን የመሳሰለ ካራሱ አልፎ የአፍሪካ ንጉስ ነኝ የሚልን አምባገነን ለመጣል ሊቢያዊያን ቢታጠቁ የሚገርም ላይሆን ይችላል፡፡ ተገቢም ሊደረግም የሚገባው ነበር ማለትም ይቻላል፡፡ በግብጽም በተመሳሳይ መልኩ፡፡

በተለይ ደግሞ ቀደም ሲል ያነሳነው ህዝቡን ያሳተፈ ምርጫ እና መሰል መብቶች በሌሉበት ጥያቄው ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ያግዛል፡፡

እንዲህ ያለው ክስተት በዓለም ላይ አዲስ ነገር ነውም ተብሎ አይታሰብም፡፡ በሃገራችንም በንጉሱ ጊዜ የተከሰተና የህዝብ መዓበል ያጥለቀለቀው ተቃውሞ ተነስቶ ንጉሱን ከስልጣን እስከማውረድ የደረሰ አጋጣሚ ተከስቷል፡፡

እኔን ያልገባኝ ግን የግንቦት 7 ተንታኞች አሁን እያሉን ያሉት፣ በተጨባጭ ሃገራችን ውስጥ ዛሬም የሃይለስላሴ ስርዓት ያለ እያስመሰለሉት ነው፡፡

በህዝብ ያልተመረጠ አምባገነን ፈላጭ ቆራጭ ስርዓት፣ ኢኮኖሚውን የሚበላ ጦረኛ መንግስት፣ ዜጎች ተጨቁነው የሚኖሩበት ሃገር፣ ዜጎች በሃገራቸው የሚሳቀቁበት እና ለመሪያቸው የሚሰግዱበት ስርዓት ከተቀበረ ሩብ ክፍለ ዘመን ማለፉም ማስታወስ የሚጠበቅብኝ አይመስለኝም፡፡

ዘመኑ ካልተለያዩ በቀር እኛ አሁን አረቦቹ ሲያካሂዱ ያየነውን አይነት ስርዓት ካስተናገድን ትንሽ ቆየት ያልን አይመስላችሁም፡፡

ትላንት የሆነውን አንድነቱን ደግሞ አስቡት፡፡

በግብጽ ለምሳሌ ሙባረክን ከስልጣን ያስወገደው የህዝብ ማእበል የስልጣን ባለቤት አልሆነም፡፡ የህዝቡን ድምጽ አከራሪው የሙስሊም ወንድማማቾች ነጥቆ ስልጣን ያዘ ማለት ነው፡፡

ልክ እንደዚህ ሁሉ እኛም ጋር ንጉሱ በህዝብ ማእበል ወንበራቸው ሲነቃነቅ ወታደሩ ገለበጠውና ለ17 ዓመት ያህል ቁጭ አለበት፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያዊያን ከእንዲህ ያለው የህዝብን ቅሬታ መሰረት አድርገው ወደሚሄዱ ረብሻና ብጥብጦች ያልተማረ ይመስላችኋል!!

ሌላውን ተውት፤ በ97 ምርጫ የፓለቲካ ግለቱ ሲጨምር፣ ትናንሽ የህዝብ ቅሬታዎችን በማጋጋል ለተቃዋሚው ጭብጨባው የደመቀ ቢመስልም ሃገር እንዲመራለት የሚመርጠውን ግን ህዝቡ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡

እናንተ ግን እንደፈለጋችሁ የምትጠመዝዙት ይመስል ግብጽ እንደሆነው፣ ልክ ቡርኪናፋሲ እንዳደረጉት፣ ልክእዚያ ሊቢያ እየሆነ እንዳለው ሁሉ ተነሱና ጦር ስበቁ የምትሉ ጅሎች ናችሁ፡፡

በጣም የሚገርም እኮ ነው፤ ይኸ ኮ ህዝብ ከመናቅ ተለይቶ የማይታይ የደንቆሮ ስራ ነው፡፡

አመጽን እንደጅረት ከሰሜን ወደ ሰሜን ምእራብ እያስጓዛችሁ “ከዚያ አቅጣጫው ወደ ምስራቅ ነው” የሚል ትንታኔ ምን የሚሉት እንደሆነ አልገባኝም፡፡

አሁን ሃገሪቱ አላደገችም፣ ለውጥ የለም፣ የህዝቡ ኑሮም አልተሻሻለም፣ ሰላምና ዴሞክራሲም የለም በሚል አይደል ይኸ ሁሉ የቀለም አቢዮት የማቀጣጠል ሂሳብ!

እንግዲህ ለአመጽ እንዲነሳ የምትጠሩት ህዝብ ይህንን የምትሉትን ሁሉ በቅርብ ሆኖ የሚያይ እሱ ነውና በተጣራችሁ ቁጥር የሚሰጣችሁ ምላሽ ምን እንደሆነ እያያችሁት ነው፡፡

ባለፈው በስቴት ዲፖርትመንት እንዳያችሁት አንዳንዴ ቢቃወማችሁም ባብዛኛው ግን እንደስታንድ አፕ ኮሜዲ እየሰማ ከልቡ የሚስቅበት የፈጠራ ቀልድ ነው የምታቀርቡት፡፡

በነገራችን ላይ የሃገራችሁን ነባራዊ ሁኔታ ማወቅ አቅቷችሁ ጦር ጦር የምትሉ በድንግማ የምትኖሩ ጽንፈኞች የሃገራችሁን ተጨባጭ የልማትና የዴሞክራሲ እድገት ለማየት ጊዜው አሁን ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

ምክንያቱም የኢትዬጵያ አየር መንገድ ከ1500 - 1700 ብር አካባቢ የነበረው የሃገር ቤት የአውሮፕላን ትኬት ዋጋውን በከፍተኛ ደረጃ አውርዶታል፡፡ ስለዚህ 600 ብር አካባቢ ገብቷልና አቅሙ ካላችሁ እናንተ ስትፈረጥጡ ትታችኋት የሄዳችኋትን ኢትዬጵያን ሳይሆን የበለጸገች ኢትዬጵያን ማየት ትችላላችሁ፡፡

ይኸ እንግዲህ ከተፈረደባችሁ ውጭ ያላችሁትን ማለቴ ነው፡፡ ለነገሩ እናንተም ብትሆኑ እዚህ እድሜ ልካችሁን የሻእቢያ ተላላኪ ሆናችሁ የህሊና ባሪያ ከምትሆኑ እንደ አንዳርጋቸው ሃገራችሁን አይታችሁ እፎይ ብትሉ ሳይሻል ይቀራል፡፡

በነገራችን ላይ ከምር ነው የምላችሁ ይህንን የአየር መንገዱን የቅናሽ አጋጣሚ ብትጠቀሙበት ጥሩ ነው፡፡

ጽናት ራዲዮ የሚቻለውን  ድጋፍ ሊያደርግላችሁም ዝግጁ ነው፡፡

እና ብዎቻችሁ ይህንን እድል አይታችሁ ብትመለሱ አሁን የፉከራ ዘፈን እየጋበዛችሁ ፉኖ ተሰማራ ስትሉ ህዝቡ ለምን ዝም ብሎ እንደሚታዘባችሁ ያኔ በደንብ ይገባችኋል፡፡

በእርግጠኛነት የምነግራችሁ ግን ኢትዬጵያ ውስጥ አሁን እናንተ እንደምታስቡት እንደአረቡ አቢዬት እንደተካሄደባቸው ወይም እንደሌሎቹ ህዝቡ ለባለስልጣናት የሚሰግድበት ስርዓት ያከተመው ድሮ እናንተ በምታደንቋቸው አምባገነን መሪዎች ዘመን ነው፡፡ ዛሬ እኔ እስከማውቀው ሰው ስልጣን የሚይዘው ህዝብ ለማገልገል እንደሆነ ማመን የሚቻለው በማየት ወይ ደግሞ ያዬትን በማመን ብቻ ነው፡፡

የምትመኙትን የሚፈጽም ህዝብ አለ መስሏችሁ ከሆነም እሱ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ኢትዬጵያዊያን ዛሬ ሰላማቸውን የሚጠብቁት ራሳቸው ናቸው፡፡ ሰላም ማስጠበቅ የመንግስት ተግባር ብቻ ከመሰላችሁ ተሳስታችኋል፣ ሃገር መገንባት የባለስልጣናት ስራ ከመሰላችሁም እንዲሁ፡፡

በሃገር ጉዳይ ላይ ኢትዬጵያ ውስጥ የማያገባው አሸባሪና ተላላኪ ብቻ ነው፡፡

በእርግጥ ይህንን ስል ሃገር ውስጥ ባሉ ተቃዋሚዎች ውስጥም የግንቦተኞችን አጀንዳ የሚያስፈጽሙ ሶስተኛ ደረጃ ተላላኪዎች የሉም እያልሁ አይደለም፡፡

ለምን መሰላችሁ ሶስተኛ ደረጃ ያልሁት፡፡

ሻእቢያ ለሌሎች የኢትዬጵያ ጠላቶችና ለአለምአቀፉ የሽብር ክንፍ አንደኛ ተላላኪ ነው፡፡ እዚህ ያሉት እነ ብርሃኑ ነጋ ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ የሻእቢያ ተላላኪዎች ናቸው፡፡ሁለተኛ ደረጃው(እነ ግንቦት 7) ከአንደኛ ደረጃ ትእዛዝ አስተላላፊዎች ማለትም ከዶላር ምንጮቹ ቀጥተኛ ግኙነት እንዲኖረው አይፈቀድለትም፡፡ ይህን የሚሞክር እጣው የአንዳርጋቸው አይነት ይሆናል፡፡ እዛዝ መቀበል ብቻ!! ሁለተኛ ደረጃዎቹ ማዘዝ የሚችሉት የበታቾቻቸውን ነው - 3ተኛ ደረጃዎችን፡፡ ከነ ዶክተር ብርሃኑ ትእዛዝ ተቀብለው በዶላር ፍርፋሪ ጉዳይ የሚያስፈጽሙ ሶስተኛ ደረጃ ተላላኪዎች አዲስ አበባ ውስጥ ያሉት ናቸው፡፡

ከነዚህ ብዙዎቹ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ፕሬዘዳንቶች እና አባላት ናቸው፡፡

የሰሞኑን የአንድነት ፓርቲ ውዝግብ ለዚህ ማሳያ ነው፡፡

የፓርቲው ፕሬዘዳንት ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው ከስልጣን እንድልቅ የተደረግሁት የዲያስፓራውን ተልእኮ እንደወረደ ልፈጽምላቸው ባለመቻሌ ጫና ተፈጥሮብኝ ነው ብለዋል እኮ!!

ይህን መቼም ሳትሰሙ አትቀሩም ሁሉም ጋዜጣና ድረ ገጽ ሲቀባበለው የከረመ ወሬ ነው፡፡

በወርሃ ነሃሴ አካባቢ ምክትላቸውን ጨምሮ 5 ሃላፊዎች በኢንጅነሩ አመራር እና ብቃት ማነስ ባለመደሰት በራሳቸው ሃላፊነታቸውን ለቀቁ አሉ፡፡

ከዚያ ከሁለት ወር በኋላ ኢንጅነሩ ከስልጣን ሲነሱ ከለቀቁት አንዱ ምክትላቸው የነበሩት አቶ ተክሌ በቀለ ፕሬዘዳንት እንደሆኑ ሰማን፡፡

የሚገርመው ሌሎች ያኔ የለቀቁትም ብዙዎቹ ተመልሰው ኢንጅነር ግዛቸው ታሪካዊ ጀግና ናቸው ሲሉ ማሞካሸት ጀመሩ፡፡

የሚገርመው ግን ኢንጅነሩ ራሳቸው አዲሱ ስብስብ የአክራሪ ዲያስፓራውን ትእዛዝ የሚቀበል መሆኑን እሳቸውም በግፊት ከስልጣን መውረዳቸውን በሰንደቅ ጋዜጣ እንደተናገሩ ሰማን፡፡

እንግዲህ እሳቸው ብዙም የገንዘቡ ችግር የለባቸውም አሉ፡፡ ምክንያት የራሳቸው የኮንስትራክሽን ድርጅት አላቸው፡፡

ስለዚህ የዶክተር ብርሃኑ ዶላር ሊያማልላቸው አልቻለም ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ሂደቱ ኢንህነሩ በቡችሎቹ ተገፉ የሚል መላ ምት ይሰጣል - ኢንጅነሩ ካሉት ተነስተን፡፡

በጣም የሚገርመው ውዝግቡን ሲከታተል የቆየው ምርጫ ቦርድ ለአዲሱ ስብስብ እውቅና አልሰጠም፡፡ ህግና ስርዓት አልተከበረም ያለአግባብ ነው አዲሱ ፕሬዘዳንትና ካቢኔያቸው ወደስልጣን የመጡት የሚል ነው አሉ፡፡

እንግዲህ አንድነትና ሰማያዊ መሰል ፓርቲዎች የሚታገሉት ለኢትዬጵያ ህዝብ ነው ወይስ ለጽንፈኛ ዲያስፓራው የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡መልሱን ማንም ያውቃል፡፡

ህዝቡ ቢጠየቅ ከተግባራቸው በቅርበት ይመልሳል፣ ጽንፈኛ ዲያስፓራው ቢጠየቅም ከዶላራቸው በቅርበት ይመልሳል፡፡ ውግንናቸው ለጽንፈኛው ብቻ እንዳይመስላችሁ፣ ውግንናው በዋናነት ከዶላሩ ነው!!

ሆድ አደር ማለት ይህም አይደል አድማጮቼ፡፡

ለማንኛውም ድሃ በህልሙ ነውና የሚያልሙት ብጥብጥ እና አመጽ ሁሌም እንደመሸበት፣ መቼም የማይነጋለት መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ምክንያቱም ለውጥ የሚያጣጥም እና ከታሪክ የሚማር ህዝብ እና ጠንካራ መንግስት አለና!!